# አደርባይነታችን
# ብዙ እያስከፈለን ነው።

*(ከቀመሩ ደስ አለኝ)*

*ኢትዮጵያ ውድ አገራችን በወያኔ ማፍያ ቡድን ተወራ፣ ብሔራዊ አንድነቷ፣ አሀዳዊ ሉዓላዊነቷ፣ ታሪካዊ ክብሯ ተደፍሮና ተዋርዶ፣ አገር ተቆርሳ፣ ሃብቷ እየተዘረፈና እየተበዘበዘ፣ ለም መሬቷ እየተሸጠ፣ ሕዝቧ ተረግጦ በጠበንጃ ኃይል መብቱን ተነፍጐ፣ ፍዳውን ሲያይ እነሆ ሃያ አመት ሆነው።*

*እንደሚታወቀው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃነት የኖረ፣ ነፃነት አፍቃሪ፣ ለነፃነቱ ፍጹም ታጋይ፣ የማይደፈር፣ አትንኩኝ ባይ፣ መብቱን አፍቃሪ፣ ደፋርና ጀግና አገሩን ከውጭ ወራሪ ኃይሎችና ከውስጥ አዋኪዎች ተከላክሎ፣ ጠብቆና አስከብሮ በብሔራዊ አንድነቱ ታፍሮና ኰርቶ በፍቅር የኖረ ሕዝብ ለመሆኑ በዓለም ኅብረተሰብ ፊት በእጅጉ ያስመስከረው ሃቀኛ ታሪኩ ነው።*

*የኢትዮጵያ ሕዝቦች ምኞታቸው፣ ፍላጐታቸው፣ ሥጋታቸውና ተስፋቸው ሁሉ ተመሳሳይና ተዛማጅ፣ የወደፊት ዕድላቸውም የተያያዘና የተሳሰረ፣ የተቆላለፈም በመሆኑ ተከባብረውና ተቻችለው በጋብቻም ተሳስረው በአንድነት በመኖር አንድ ብሔራዊ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ በመሆን ያሉና የሚኖሩም የጋራ ታሪክ ባለቤቶች ናቸው።*

*ሕዝቡ ተከባብሮና ተቻችሎ አብሮ በመኖር ለመበልጸግ ፅኑ እምነትና ፍላጎት ያለው፣ ኢትዮጵያን በአንድነቷ ትልቅና ኃያል፣ በሕዝቧም ብዛት ጠንካራና ብርቱ እንድትሆን የሚያምንና የሚመኝ ነው።*

*ወያኔ ለጥ ሰጥ አድርጐ ለመግዛት የኢትዮጵያን ምድራዊ አካል ለሁለት ከፍሎ አንዱን ወዲያ ጥሎ ሌላውን አጉሮ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን ተነጥቆ፣ ሰብዓዊ ክብሩና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተረግጠው በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ ሽብር እያካሄደ ነው።*

*የአገሪቱ ኢኮኖሚም እንደዚሁ እንዲወድቅ እየተደረገ ሕዝቡ በረሃብና በስደት ላይ አለ የወያኔ የፖለቲካ ሥርዓት ኋላ ቀር ማርክሲስት ሌኒንስት ርዕዮተዓለም ዓይነት የማፍያ ቡድን ማራመጃ ሥርዓት በመሆኑ በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ የኤኮኖሚ ጥቃት እያደረሰ ይገኛል።*

*ወያኔ ትንቅንቅ የተያያዘው ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያን ለማፈራረስ፣ ለማሳነስ ወደ ከፍተኛ ችግር ርሃብ፣ በሽታ፣ ድንቁርናና ኋላ ቀርነት፣ ድክመት እንዲሰፍን ከተራው ሰውና ከሕዝብ ጋር እንደሆነ ለማንም የሚያጠያይይቅ ጉዳይ አይሆንም። ሕዝቡ በአገር ኩርቶና*

ተስፋ ኖሮት እንዳይኖር በድንቁርና እንዲዳከም ተደርጓል። የኤኮኖሚው ዘርፍ በልዩ ልዩ የቁጥጥር ሕጎችና ደንቦች በመተብተቡ ምክንያት ምርታማነት እንዲዘቅጥ፣ የሕዝቡ የመስራትና የመፍጠር መንፈስ እንዲቀዘቅዝና የሥራ ዕድሎችም እንዳይስፋፉ ሆኗል።

በተለይም ለግብርና ክፍሉ ምርታማነት መቀነስና ራስን ለመመገብ የመቻል አቅም ማነስ ለማያቋርጡ ዓመት ለአገራችን ርሃብን እያበዘ መጥቷል። ዛሬም ለም መሬቱ እየሸጠ የሚያርሰውንም እየተቀማ ገበሬው እየተሰደደ ነው። ቀሪውን ለባለ ኮንትራቱ በርካሽ ጉልበቱን እንዲሸጥ ይደረጋል። በተራ ነጋዴው ላይ የዋጋ ሽቅበት ቁጥጥር ሕገ-ወጥ ሕጎችንና ተቆጣጣሪዎችን በማሰማራት የሙስናና ያጭበርባሪዎችን ቁጥር በመጨመር ሕዝብ በይበልጥ እንዲጎዳ በችግር አለንጋ እንዲገረፉና አለቅጥ እንዲገላታ ተደርጓል።

አገሪቱ አንድ ትልቅ የእስረኞች አገር ሆናለች ሕዝቡ በአገሩ ውስጥ ሰላማዊ ኑሮውንና ሥራውን ለመስራትና ለማንቀሳቀስ እንዳይችል በክልል ተወስኖ መዘዋወር አቅቶታል። በእስር ቤቱና በማጎሪያ ጣቢያዎች ብዙዎቹ በረሃብና በበሽታ፣ በመደብደብና ቶርች አካሉ ጉሎና በአእምሮ ሰለባ እያለቁ ናቸው።

ኅብረትና አንድነትን በሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎችና የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ ከፍተኛ የጠላትነት ዘመቻ ያለማቋረጥ ወያኔ/ኢህአዲግ ከመነሻ እስከ አሁን እያካሄደ ሲሆን እንዲሁም ደግሞ በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ ልዩነትና ግጭቶችን እየበረታታ ይገኛል።

ወጣቱ ለትምህርት ያለው እድል እንዲወስን በአጭር የትምህርት ደረጃ እንዲቀር ከመደረጉም ባሻገር  በመጥፎ ባህሪዎች ሱስና ስነ-ልቦና አእምሮው እየተሰለበና እየተኮላሸ ሥራአጥ ትውልድ ሆኖ ይገኛል። ሌላም ያለ ፍላጎቱ በግዳጅ የወያኔ አገልጋይ ወታደርና የሽብርተኞች ጠባቂ በመመደብ ለወያኔ ቡድን ጥሩ የገንዘብ ምንጭና ሕውልና ጠባቂ ዘበኛ ሆኖ ይገኛል።

የተማረው አዋቂውና ጥሩ የሥራ ልምድ ያለው የሕዝብ ክፍል፣ ታስሯል፣ ተሰዷል፣ ተገሏል፣የወያኔ/ኢህአዲግ አባል ካልሆነ ሥራ ወይንም ከፍተኛ ትምህርት አያገኝም አይፈቅድለትም። ተዘዋውሮም መስራት፣ መንቀሳቀስና መነገድ መማርና መኖርንም ይነፍጋል። (የትግራይ-አድዋ ካልሆነ በስተቀር) በአጠቃላይ አገርና ሕዝብ እየተጎዱ ነው። ሕዝብ እንደባይተዋር ተደርጐ የአገሩ ባለቤትነትና ሰብዓዊ መብቱ ተነፍጐ በክልል ተወስኖ መንቀሳቀስ መዘዋወርና መስራት የማይችል፣ በሕግና በፍትህ ፊት በእኩልነት መታየትና መዳኘት፣ መተዳደሩ ተነፍጐታል። ሕዝብ በሕግ አድሎውና በፍትህ መዛባት ፖሊስና ዳኝነት

ሥርዓት ሕገ ወጥ (ሥርዓት አልባነት) እየተዳደረና ልዩነትም እየተፈጸመበት እየተንገላታ ነው። ሕዝብ፣ የወያኔ አባል፣ ደጋፊና ተለጣፊ አገልጋይ ጥቅም ሰጪ እንዲሆን ይገደዳል ካልሆነ እየተበደለ ብዙ መከራ እየተቀበለ በግፍ ሥርዓት በአደርባይነት ደካማ ሆኖ እየኖረ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱ የሌለውና ሰብዓዊ መብቱን ተነፍጎት፣ ወጣት ሴት ወንዱ፣ አዛውንቱ፣ የተማረ ያልተማረው፣ ነጋዴው ገበሬው አገሩን እየተወ ወደ ጐረቤት አገሮች አልፎ በየትኛውም ዓለም አህጉርና አገሮች እየተሰደደና እየተበተነ ከመገኘቱም ባሻገር በተሰደደባቸው አገሮች ተቀባይነትን በማጣት ለአያሌ መከራና ውርደት፣ መደብደብ፣ መታሰር፣ መገደል፣ ያለግለሰቡ ፈቃድ የሰውነት አካል መወሰድ፣ ገደል መጣል፣ ውሃ ውስጥ መክተት፣ በአየር እጦት እንዲታፈን ማድረግ፣ ለአውሬ መስጠት መሸጥም ሲሆኑ እንዲሁም ደግሞ በወያኔ አጋር አገሮች ታስረው ለወያኔ በመመለስ ለእስራት፣ ለግርፋት፣ ለግድያ መዳረግን የመሳሰሉት የስቃይና የመከራ ችግሮች ሕዝብ በግፍ ፍዳውን እያየ በአደርባይነት ብዙ እየከፈለ ነው።

ወያኔ/ኢህአዴግ ሕግን የማያውቅ፣ ለሕግ የማይገዛ፣ አጋሚዶ፣ ፀረ-ኅብረተሰብ፣ ፀረ-አንድነት ባህሪ ያለው በቋንቋ ልዩነት ተመስርቶ ጎጠኛ ከፋፋይና የማፍያ ሥርዓት አራማጅ ነው። ወያኔ የትግራይ ነፃ አውጪ ሆኖ የተነሳና ያለ በሽብርና በደም ጐዳና ተጉዞ ቅራኔና ጥላቻን አንቀሳቃሽ የውስጥ ወራሪ ኃይል ሲሆን እንደሚታየው ሌላውንም በቋንቋ ልዩነት እንዲጋጭ፣ እንደ ጠላት ማየትና ማጥፋት ወይንም በበላይነት በመቆጣጠር በኢትዮጵያ ላይ የፈለገውን ማድረግና ሃብቷን፣ ቅርሷን መዝረፉ ዋና አጀንዳው ያደረገ ቡድን ነው።

ይኸም ለመሆኑ ወያኔ/ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን ሁሉ በጠላትነት የሚፈርጅ ለአመጽና ለጦርነት የሚገፋፋ የፖለቲካ ጠላት እንጂ የፖለቲካ ተፎካካሪ ወይንም አቻ ተወዳዳሪ የማያውቅ አጥፊ የማፍያ ቡድን ሲሆን በራሱ ዙሪያ ያሉትን፣ አባላቱን እንኳን ሳይቀር የማይጠቅሙትና የሚቀናቀኑት ከሆነ በጭካኔ የሚያባርር የሚገል አረመኔ የሽፍታ ኃይል ቡድን ነው። ለዚህ መረጃ የወያኔን ታሪክ መገንዘብና አቶ መለስ ገና ከጅምሩ አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ የተናገረው "እኛን (እነ አቶ መለስን) ለመቃወምና ለመዋጋት የምትፈልጉ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ" "ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ እንደፈለጋችሁ ሁኑ" ያለውና "ከእንግዲህ ኢትዮጵያ ከእኛ እጅ አትወጣም" የተባሉት የፉከራና የእብሪት አነጋገሮች ለምሳሌነት ይጠቀሱ እንጂ አያሌ የአጥፊነት ባህሪዎችና ተግባራት ሞልተዋል።

ለአገርም፣ ለሕዝብ፣ ደንታ እንደሌለው በወያኔ ቡድን የተነገረን ገና ከጅምሩ ጥንት ሲሆን ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በታጋሽነት ባህሪው በትዝብት በዝምታ ይህን ያህል ግፍና መከራ እየተቀበለ እስከ አሁን አለ። ለምን?

ወያኔ፣ አቶ መለስና ቡድኑ የሥልጣን አምልኰና አምባገነንነት ያለው ዋናውና ሃቁ ባህሪ አሸናፊ መሆንና በስልጣን ላይ ቆይታን አጠንክሮ የጥፋትና የዘረፋ አጀንዳን ማራመድ በመሆኑ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ሁሉ በጠላትነት መፈረጅ፣ ማሸነፍና መቆጣጠር ሆኖ በየምርጫዎቹ እንደታየው የሕዝብን ምርጫ ድምፅ መዝረፍና ማጭበርበር፣ የሕዝብን መብትና ፍላጐት ፋይዳ ቢስ አድርጐ በአገሪቱ ላይ አንፈራጦ ምክር ቤቱን ተቆጣጥሮ ይገኛል። ወያኔ አጀንዳውን ለማራመድ አንድ ብቸኛና ሁሉን አዋቂ፣ አድራጊና መሪ አውራ ድርጅት ነኝ ብሎ በአገርና በሕዝብ ላይ እየፈነጨ ተቆጣጥሮ ለም መሬቷን እየሸጠና ሕዝቧን ለርሃብ፣ ለበሽታ፣ ለስደት ለመሸጥም ዳርጐት ሕዝብ ይህን ጭቆናና ግፍ በአደርባይነት በድክመት እየጠበቀ ያገር ያለህ እያለ አለ።

ወያኔ በውሸት ዲሞክራሲ ብዙ ድርጅቶችን በራሱ አምሳያ ሲፈጥርና ሲያዳቅል እንዲሁም በየድርጅቶቹ መሃከል እየገባ እርስ በርስ ሲያጣላ፣ ሲያበጣብጥ ሲያከፋፍል የብዙ ሰዎችን እልቂት እስራትና ስደትን የእርስ በርስ ጥላቻና ጠብን፣ መሰዳደብና መደባደብን ውሸትና ሃሰትን የፖለቲካው ባህል እንዲሆን ፈጥሯል።

በኢትዮጵያ ሕዝቦቹ ላይ በቋንቋ ልዩነት በየቦታውና በየሁኔታው በተለያዩ ጊዜዎች ግጭቶችን አቀጣጥሏል። የተመላለሰ ችግር ርሃብ፣ መታረዝና በሽታ እንዲደርስ በሰው ዘራሽነት እንዲፈጠር በሰፊው እየተደረገ ነው።

እንደዚሁም ለተራበውና ለተጎዳው ወገን ከውጭ የመጣውን የእህልና ሌላ ርዳታዎችን በመሸጥ ጥሬ ገንዘቡን ለወያኔ ድርጅት እንዲውል ተደርጓል። የውጭ እርዳታና ብድር ገንዘብ ለራሱ ለወያኔ ውሎአል። ሕዝብ እየተራበ የአገሪቱ ለም ድንግል መሬትዋ በኮንትራት በርካሽ እየተሸጠ መሬቱ እየተጐዳ ደኖችዋና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶችዋ እየተራቆቱ ከመሆኑም ባሻገር የቆሻሻና የመርዝ ፋሳሽ መውደቂያ እየሆነ ነው። ለም መሬት በኮንትራት ሲሰጥ የተገኘው ገንዘብ ለምን አገልግሎት ዋለ? ለወያኔ ግል ኪስ!

ንፁህና በርካታ የውሃ ሃብታችን ወንዝ፣ ጅረቱ ሁሉ በመርዝ እየተበከለና እየቆሸሸ እንዳልነበር ሆኖ ለመጠጥና ለሌላ አገልግሎትም እንዳይሰጥ በመሆኑ በውሃ በሽታ የሚሞተው ሕዝብ ቁጥር የትና ለሌ እየሆነ ይገኛል። የአገር ውስጥ ማዕድኖች ሳይቀር ለውጭ ባለሃብቶች በጨረታ እየተሸጠ እየተቸረቸረ ነው።

ኢትዮጵያ ለዘመናት ያካበተቻቸው የአገር ሃብትና ቅርሶች፣ በተራድኦ ያገኘቻቸው ንብረቶች ሁሉ ተዘርፈዋል። የተዋዋለቻቸው ውሎች ፈርሰው ሕጋዊነት አጥተዋል። የአገር ሉዓላዊነት ዳር ድንበር የየብስ፣ የውሃና የአየር ክልሏ እየተጣሰና ፈርሶ እንዲሁም ሰንደቅዓላማዋ ክብር እየተነካና እየተዋረደ ይገኛል።

የአገር በተለይ የውጭ ገቢያ የሚያስገኘው (የሚሸጡ) ቁሳቁሶች የወያኔ አባላት የግል ሀብት ሆኖአል። የመሬት ይዞታ በአጠቃላይ የወያኔ/ኢህአዲግ አባላት ካድሬዎች የግል ሀብት ሲሆን በአገሪቱ ውስጥ ያሉ የማምረቻና ፋብሪካዎች ባንኮች ወዘተ… የወያኔ ማፍያ ቡድን ነው። በታክስና በተለያዩ ግብር የሚከፈለው ለሕዝብ ደህንነትና አገልግሎት ሳይሆን ለወያኔ ነው።

ከዚህ በላይ ከብዙ በጥቂቱ የተዘረዘሩት ጥቃቶች፣ ችግሮች፣ ብሶቶችና ሰቆቃቆች በሚያነሆልል መልኩ የወያኔ ማፍያ ካድሬዎች ማነፍነፊያ፣ የዋህ፣ ያንገዋለሉት የሚሞጫለፉበት ኅብረተሰብ ሆነን በአደርባይነት ስንቀበለው ቆይተናል።

ከእንግዲህ የሚሰማህን ሰቆቃ በቃ ልትል ይገባሃል። ከጣላት ጋር መፋጠጥን የአገር ባለቤትነትንና የዜግነት መብትን፣ ሃብት፣ የማንነት ኩራት፣ ክብርን ለማስጠበቅ ሁሉም ለክብሩ፣ ለአገሩ ሆ ብሎ መነሳት ገድሉን፣ ጀግንነቱን የሚያሳይበትና አገሩን የሱነቱን የሚያረጋግጥበት ወቅት መሆን አለበት። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሕግ የበላይነት የሕዝብ መንግሥት ለማምጣት ግዴታውም ኃላፊነቱም ነው።

ከኢትዮጵያዊ ወግ የወጣ ክብርና ኩራት የጐደለውና ያነሰው ይህ ትውልድ ሊሆን ከቶውንም መዛነፍ፣ ከዓላማው መዘናጋትና መሳሳት ሊኖር አይገባም። የዚህ ትውልድ ሰዎች ልንሆን ግዴታም በጐነትም የሚጠይቀን የነዚያ የቀድሞዎቹ ትውልዶች ሲወልድ ሲዋለድ ያመጣን ዘር ዛሬም ነገም ከዚያም ለዘመናት ሊኖር የሚገባው ኃላፊነት አለብን።

በአደርባይነት ደካማ ሆኖ መገኘት ይብቃን በቆራጥነት በፍጥነት እንነሳ፣ እስከ ድልም እንፅና::

*ሕዝብ ያሸንፋል*

*ምንጊዜም ኢትዮጵያ*